የለጋሽ አገሮች አምባሳደሮች ቡድን መግለጫ

ጥቅምት 24 ቀን 1998 ዓ.ም

ከጥቅምት 22 ቀን ጀምሮ በኢትዮጵያ የደረሱ ሁኔታዎች

የለጋሽ አገሮች አምባሳደሮች ቡድን ከጥቅምት 22 ቀን ጀምሮ አዲስ አበባ ለተከሰተውና በሰው ሕይወት ላይ ሞትና ጉዳት ባስከተለው አለመረጋጋት የተሰማውን ጥልቅ የሆነ ሥጋት መግለጽ ይወዳል፡፡ ሞትና ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች ሐዘኔታችንን እንገልጻለን፡፡ በጸጥታ ኃይሎች ሆነ ወይም ትዕይንት በሚያደርጉ ወገኖች የሚፈጸሙትን ሁከቶች ሁሉ፣ በተለይም ሞትን የሚያስከትሉ ማናቸውንም መሣሪያ መጠቀም ያሳዝነናል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በሰኔ 2 ቀን 1997 ዓ.ም እንደደረሱት ሁሉ መንግሥት ቃሉን በሰጠው መሠረት በገለልተኛ ወገን በአስቸኳይ መመርመር ይኖርባቸዋል፡፡

በርካታ ፓርቲዎች በሚኖሩበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በፖለቲካ አመራሮች መካከል በገንቢነት አብሮ መሥራት ያለ በመሆኑ፣ የቅንጅት ፓርቲ መሪዎችና አንዳንድ የሲቪል ማኅበረሰብ ኃላፊዎችም በመታሠራቸው የለጋሽ አገሮች አምባሳደሮች ቡድን የተሰማውን ከፍተኛ ሥጋት ይገልፃል፡፡ የፖለቲካ ታጋቾች በሙሉ መፈታት አለባቸው፡፡ የታገቱት ሁሉ በሕገ መንግሥቱ መሠረት የሕግ ጥበቃ እንዲደረግላቸው እና ክስ ካልተመሰረተባቸውም በአስቸኳይ እንዲፈቱ የለጋሽ አገሮች አምባሳደሮች ቡድን ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ በዓለም አቀፋዊ አፈጻጸም መሠረት ለታገቱት ወገኖች መድኃኒቶችና ሌሎችም ሰብዓዊ እርዳታዎችን እንዲያገኙና ከቤተሰቦቻቸውም ጋር እንዲገናኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ቅንጅትም በበኩሉ ሰው በኃይል መጠቀምንና ፍጥጫን በማስወገድ፣ ሕግንና ሕገ መንግሥቱን እንዲያከብር ማበረታታት አለበት፡፡ ሁሉም የፖለቲካ ቡድኖች በፓርላማና በማዘጋጃ ቤት ዲሞክራሲያዊ ሂደት እንዲሳተፉና የኢትዮጵያና ዲሞክራሲያዊ ተቋሞች ለማጠናከር ወደ ሁለትዮሽ መደራደር እንዲመለሱ የለጋሽ አገሮች አምባሳደሮች ቡድን ያበረታታል፡፡ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞን ማሳየት በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ሕጋዊ መብት ቢሆንም፣ በፀበኝነት የታጀቡ ትዕይንቶች በሕዝብ ደህንነት ላይ ከፍተኛ አደጋን ከሚያስከትሉ በቀር ዲሞክራሲን ወደፊት ለማራመድ ምንም አይፈይዱም፡፡

በሁለቱም ወገን ከፍተኛ ታጋሽነት እንዲኖር እና ወደ መረጋጋትና ሰላማዊ የሁለትዮሽ መደራደር እንዲመለሱ የለጋሽ አገሮች አምባሳደሮች ቡድን አጥብቆ ይጠይቃል፡፡